# ለተከበርከው ምርጥ ኢትዮጵያዊ ክቡር አቶ ጌታቸው ረዳ

ለኢትዮጵያዊያን ድረገጽ አዘጋጆች፤

ለወንድም ጌታቸው ረዳ የኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ ያስተላለፍኩለት ይህች ማስታወሻ በድረገጻችሁ እንድታሳትሙልኝ ልኬአለሁ። ለትብብራችሁ አመሰግናለሁ።

ቀን ያዘነበለባትን፤ የታሪክ ግድፈት የተፈፀመባትን፤ልጆቿ የከዷትን፤ የሩቅና የቅርብ ጠላቶቻችን ጊዜ ጠብቀው የከበቧትን የዛሬዋን ኢትዮጵያ ከገባችበት ወጥመድ ለማውጣትና ለማዳን አንተ የምትከፍለውን ኢትዮጳያዊ አርበኝነት ለማድነቅ ብቻ ሳይሆን ይልቁንም እንደመርህ በመቀበል በንቃት በመከታተል ላይ የምገኝ ወገንሕ በመሆኔ የሐገር ኩራትና መመኪያ ስለሆንክ ይችን አጭር ማስታወሻየን እንድፅፍልህ ስሜቴ አስገድዶኝ መቆጣጠር ባልቻልኩት የደስታየ ብዛት ተወጭ ከመቀመጫየ ብድግ ብየ ከጉልበቴ ሸብረክ በማለት ለታለቁ የቁርጥ ቀን ልጅ ያለኝን አክብሮት በኢትዮጵያዊነቴ በታለቅ ትህትና ስገልፅልህ ኩራት እየተሰማኝ ነው።

<u>ክቡርነትህ</u> ፦ ከሁሉም በላይ በትግሉ ውብስብነት ምክንያት ተማርኩ የሚለው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ አገርና ሕዝብ እየጠፋ መሆኑን በአይነ ህሊናው እየተመለከተ ዝምታን በመረጠበት ጥቂቱ ደግሞ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ቆርጠው ከተሰለፉ ሐይሎች ጋር አብሮ ዳንኪራ በሚመታበትና በሁለት ካራ በሚበላበት በዚህ አስተዛዛቢ ወቅት አንተ ግን ኢትዮጵያ!!ኢትዮጵያ!! ኢትዮጵያ!! በማለት ድምፅህን ከፍ አድርገህ በመጮህ ይኸውና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማዳኑን ወቅታዊ ጥያቄ አንግበሕ የትግላችን ጉዞ ምህዋሩን እንዳይስት በእውነታ ላይ የተመሰረተና ወደ እውነታነት የሚጓዝ የሕሊና ትጥቅ እያስታጠቅከን ስለሆነ የዘመናችን ዘራይ ደረስ ወይም የዘመናችን ቴወድሮስ ነሕና እንኮራብሐል እንመካብሐለን።

በመጨረሻም ይሕ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማዳን ግዙፍ ጥረትሕ ፍሬ አፍርቶ የምትናፍቀውን አገርህንና ክቡር ሕዝብህን በታሪኩና በነፃነቱ የሚኮራ የማይደፈር ሐያል ሕዝብና አገር እንዲኖረን ነውና ቅን ኢትዮጵያዊ ጥረትህ ለሁላችን ትምህርት ሰጭ ሆኖ የምሳሌነትህ ደምህ ከደማችን፤ ሕሊናህ ከሕሊናች እንዲዋሐድ የፈጠረንን አምላክ እየለመንኩ ለተወደድከው የዘመኑ ቁርጥ ቀን አርበኛችን ጤና እና ሰላም እመኛለሁ።

መሰረት ቀለመወርቅ
አውስትራሊያ